ሳምንታዊ ዜና ዘገባ (ሐምሌ 12 ቀን 2001 ዓ. ም.)

**የወያኔው አስቸኳዋይ ስብሰባ ለቀናት ተራዘመ፣ ለአዳዲሶቹ ካድሬዎች መሬት እንዲታደላቸው ወሰነ፣ ኦህዴድ ውስጥ ችግር መፈጠሩ ተጠቆመ፣ ለፖለቲካ ስልጠና ወደ ፍቼ ከተማ የተላኩ መምህራን ተመለሱ፣ ለመምህራን ብቻ የደሞዝ ጭማሪ ተደረገ >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ-ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ .............**

የወያኔው ቡድን የእርስ በእርስ ሽኩቻው እያየለ በመምጣቱ መፍትሄ ይሆናል በማለት የተለያዩ እርምጃዎችን ቢወስድም ችግሩ እየሰፋ መምጣቱን የሰሞኑ አስቸኩዋይ ስብሰባዎች አመላካች መሆናቸውን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ገለጹ::

የወያኔ ማእከላዊ ኮሚቴ አስቸኩዋይ ስብሰባ ሐምሌ 4 እና ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በማድረግ ላይ እያሉ በተለጣፊዎቹ ድርጅቶች ውስጥ ደግሞ የተጋጋለ ነገር ተከስቶዋል በሚል የአዲስ አበባው ስብሰባ ተቁዋርጦ ኦህዴድ በናዝሬት ከተማ ላይ አስቸኩዋይ ግምገማ ላይ የተቀመጠ ሲሆን፤ የህዝቡን እና የበታች ካድሬዎቻቸውን ትኩረት ለማስቀየር ሲባል የአመታዊ ያልተቁዋጨ ግምገማ በሚል የተቀመጡ መሆኑን ይኸው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

የናዝሬቱ የኦህዴድ አስቸኩዋይ ስብሰበባ ሰኞ ሰኔ አንድ ቀን 2001 ዓ.ም. የተጀመረ ቢሆንም እስከ ሃምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም. ድረስ የቆየ ከመሆኑም በላይ ስብሰባው ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ እርስ በእርስ በንትርክ የተሞላ ነበር ያለው ዘገባ በተለይ ወጣት የፓርቲው አባላት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚደርሰው በደልና ግፍ የሚያበቃበት ቀን መቼ ነው? እስከ መቼስ የእኛ አንጡራ ሃብት እየተሙዋጠጠ ለግለሰቦች ኪስ ማደለቢያ ይሆናል? በአንድ ሃገር እንዴት ሁለት ህግ ተግባራዊ ይሆናል? የሚልና ሌሎችንም ጥያቄዎች ያነሱ ሲሆን የመድረኩ መሪ አባዱላ ገመዳ እና ግርማ ብሩ እየተጋገዙ የወጣቶቹን ሃሳብ ለመምታትና ለማከሎላሽት ሲራወጡ እንደነበረ ዘገባው አብራርቶዋል::

በየግዜው ሲበጠስ ሲቁዋጠር የመጣው የወያኔ ተለጣፊ ድርጅት ካድሬዎች ሙግት በውስጣቸው የአንድ ወቅት ትኩሳት ሆኖ ይቆይና ወዲያውኑ እየቀዘቀዘ የሚመጣ ሲሆን ይህም የዛሬው ትርምስና ፍትጊያ ከወትሮው ያልተለየ ነው ያለው ዘገባ በዚህ በሰሞኑ የተነሳው አተካሮም ከስራ እስከ መባረር እና ከደረጃ ሊያስነሳ የሚችል የወንጀል ታርጋ እስከመለጠፍ ደረጃ ተደርሶ ገለል የሚደረጉበትን ዘዴ በመቀየስ የተንኮል ሴራ መረቡ ሲተበተብ እንደነበር በቅርበት የሚያውቁትን ሰዎች እማኝ አድርጎ አስረድቶዋል::

በአሁኑም ስብሰባ ላይ ወከባና ግርግር ሲፈጥሩ የነበሩትን ካድሬዎች በቡድን ተከፋፍለን እንወያይ በሚል በቀላሉ ምንጠራ ያደረጉባቸው ሲሆን ከስብሰባው በሁዋላም የተለያየ ወንጀል ተለጥፎባቸው

ወደ ዘብጥያ ለማስገባት ሴራ ተጠንስሶ ለተግባራዊነቱ ህሊና ቢስ ሆድ አደሮች መሰማራታቸውንም ለማወቅ ተችሎዋል::

በተለይ በአስቸኳዋይ ስብሰባ ላይ ካድሬዎቹ ያነሱዋቸው ጥያቄዎች የወያኔውን ከፍተኛ ባለስልጣናት ግርማ ብሩና አባዱላ ገመዳ መመለስ ያልቻሉት ቢሆንም ለውይይቱ ስኬታማነት በቡድን በቡድን እንከፋፈልና እንወያይ የሚል ማምለጫ ሃሳብ አምጥተው የካድሬዎቻቸውን አቁዋም ለማስቀየር እንደቻሉ ዘገባው ጨምሮ ገልጦዋል::

እነ አባዱላ በቀላሉ ጥያቄውን አዳፍነው ማስቀረት ከመቻላቸውም በላይ መዳፈኑን በማይፈልጉት ላይ ከስራ ዝውውር እስከ እስራት በሚደርስ እርምጃ ወስዶ ጥያቄውን እስከ ወዲያኛው አዳፍኖ ለማስቀረት እንደሚቻል መዶለታቸውን የታመኑ ውስጥ አዋቂዎች ያስረዳሉ :: በአሁኑም ስብሰባ ላይ ወከባና ግርግር ሲፈጥሩ የነበሩትን ካድሬዎችን በቡድን ተከፋፍለን እንወያይ በሚል በቀላሉ ምንጠራ ያደረጉባቸው ከመሆኑም በላይ ከእንግዲህ ወዲ እንዲህ ዓይነት ጥያቄ የሚያነሳ ካድሬ ቢኖር የማያዳግም እርምጃ እንደሚወሰድበት መግለጻቸውም ታውቆዋል::

የኦህዴድ አስቸኩዋይ ስብሰባ ከመደረጉ አስቀድሞ ቅዳሜና እሁድ እለት በወያኔ ማእከላዊ ኮሚቴ ውስጥ ተድርጎ የነበረው ስብሰባ ላይ ስለ አዳዲስ ካድሬዎች ድልድና ጥቅም ማስጠበቅ እንዲሁም አዲስ አደረጃጀት ላይ የተወያዩ መሆኑን የገለጸው ዘገባ በተለይ መለስ ውጭ ሃገር በነበረበት እለት የተነሳው አጀንዳ ለአዳዲስ ካድሬዎች መሬት እንዲሰጥና በጥቅም ማሸነፍ በሚለው ላይ ውይይት እንደተረደገበት አስረድቶዋል::

በህዝብ ሃብትና ንብረት ያሻቸውን እየፈጸሙ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት እስከዛሬ በራሳቸውና በዘመድ አዝማዶቻቸው ስም መሬትና ገንዘብ ሲያድሉና ሲዘርፉ የነበረ ሲሆን ፤ አሁን ደግሞ በጥቅም ሆዳቸው አቸንፎዋቸው አባል ለሚሆኑት እና ህዝባዊ ተቃውሞውን እንዲዳፈን ሊያደርጉ ለሚችሉ ካድሬዎች አፍ ማስያዢያ የሚሆን በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር ገንዘብ በበጀት ደረጃ እንዲያዝ ሃሳብ መቅረቡና መወሰኑን ለማወቅ ተችሎዋል::

ገንዘቡ ለካድሬዎቹ ሲሰጥ እንዴትና ለምን የሚል ጥያቄ መነሳቱ ስለማይቀር በብድር መልክ እንዲደርሳቸውና የሚፈቀደው በጀትም በአበዳሪ የማይክሮ ፋይናንስ ተቁዋማት ውስጥ ገቢ ተደርጎ ሽፋን እንዲሆን ጭምር ውሳኔ ላይ ማረፉንም ለማወቅ ተችሎዋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በመጪው ምርጫ ላይ ከፍተኛ ባለስልጣናት ተወዳድረው የምክር ቤት ወንበር ይያዙ ወይስ በምትካቸው አዳዲሶቹ ካድሬዎች ይሁኑ በሚለው ላይ ውይይት ያደረጉ ቢሆንም ለግዜው እርስ በእርስ መስማማት ጠፍቶ ያለ ውሳኔ የተበተነ ቢሆንም በቅርቡ እንደገና እንደሚመክሩበት የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ወያኔ በህዝብ ላይ እየፈጸመ ባለው አሰቃቂ የግፍ ተግባር የተነሳ ከህዝቡ ጋር ከፍተኛ ጥላቻ ስላተረፈ ነባር ካድሬዎቹን በአዲስ ቀይሮ ለማታለል እንዲያመቸው ለጀመረው ዘመቻ ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በተለይ ከበረሃ መጣን የሚሉት ጽንፈኞች ደማችንን አፍስሰን ፤ አጥንታችንን ከስክሰን ፤ ቆስለንና ተርበን የመጣንበትን እንዴት እንደዋዛ ከተማ ለከተማ ሲያውደለድል ለነበረ ሃይል እናስረክብ በሚል ብርቱ ተቃውሞ እያሰሙ ሲሆን ፤የወያኔ ማእከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይም ይኸው ጉዳይ ተንጸባርቆ ሳያስማማቸው እንደቀረ ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል።

ወያኔ ለ18 ዓመታት ህዝብን ፍዳ ሲያሳይ የኖረ ፤ ሃገሪቱዋን ዙሪያዋን እየቦረቦረ የነበራትን ዝና እና አኩሪ ታሪክ እያሳነሰ እና እያኮሰሰ ከብጥስጣሽ ሃገራት በታች ለማድረግ ከመጣሩም በላይ አጎራባች ባሉ አገራት የዘላቂ ጠላትነት ዘመቻ እንዲከፍቱ በማድረግ ከኬንያ ፤ ከሶማሊያ ፤ ከሱዳን ፤ ከኤርትራ እና ከሌሎችም ህዝቦች ጋር መልካም ወዳጅነት እንዳይኖር እየሰራ ከመሆኑም በላይ መሪው መለስ ዜናዊ ጨምሮ ስልጣን እለቃለሁ እያሉ ህዝቡን ለማታለል ደጋግመው እየዋሹ መሆኑን ያስታወሰው ዘገባ አሁንም የበፊቱ ውሸታቸው አልበቃ ብሎዋቸው በማእከላዊ ኮሚቴ ደረጃ ትልቅ ክህደት እና ሸፍጥ ለመስራት እየተራወጡ እንደሚገኙም  ጨምሮ ገልጦዋል።

በተያያዘ ዜና ወያኔ ከህዝብ ያጣውን ድጋፍ ለማግኘት በሚል አዳዲስ ምልምል ካድሬዎች ወደ ተለያዩ የፖለቲካ ማሰልጠኛ ካምፖች እየላከ የአስራ አምስት ቀን ስልጠና እየሰጠ ማሰማራት መጀመሩ ታወቀ።

ሰሞኑን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በቴክኒክና ሙያ ተመረቁ የተባሉ ተማሪዎችን እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን መሃከል ቀድመው የወያኔ አባል የሆኑትንና ደጋፊ መሆናቸው የተረጋገጠላቸውን መልምለው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ እና ወደፊት ምን መሰራት አለበት በሚሉና ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘለዓለማዊ ብቸኛ ፓርቲ እንዲሆን በሚሉ የፖለቲካ ስብከቶች ዙሪያ ያጠነጠኑ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ መደረጉ ታውቆዋል።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በሙያ ብቃታቸው በተማሪዎቻቸው ዘንድ ትችትና ወቀሳ የሚደርስባቸውን በተለያዩ ሱሶች የተጠመዱትን በቀላሉ አንድ ግዜ ሲጠሩዋቸው አስር ግዜ አቤት የሚሉትን መምህራን መልምለው የካድሬነት ስልጠና ለ15 ቀናት ፍቼ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ወታደራዊ ካምፕ ውስጥ የተሰጣቸው መሆኑና በተጉዋዳኝ ሴቶች የልጆች እናት የሆኑ የማስተማር ብቃታቸው ዝቅተኛ የሆኑትን ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ ጎጃም በር አቅጣጫ በሚገኘው በተለምዶ አዲሱ ገበያ ቶታል ከተባለው አካባቢ ከፍ ብሎ በሚገኘው ድል በር በሚባል ትምህርት ቤት ውስጥ የካድሬነት ስልጠና ተሰጥቶዋቸው በህዝቡ ጉያ የተሰማሩ መሆናቸው ታውቁዋል።

በሁሉም ቦታ ለአስራ አምስት ቀን ስልጠና የተሰጣቸው እና የተመረቁት መምህራን ሁለት ዓይነት ግዳጅ የተሰጣቸው ሲሆን እርሱም በተመደቡበት ቦታ ሁሉ የደጋፊዎቻቸው ቁጥር እንዲጨምር እና

የስለላ ስራ እንዲሰሩ የሚል መሆኑን ስልጠናውን ከተካፈሉት ሆድ አደሮች ያፈተለከው መረጃ አረጋግጦዋል፡፡

በትምህርት ቤት ውስጥ ተመሳስለው የሚመደቡ ሰላይ መምህራን በግቢ ውስጥ እንዲሰልሉና የተቀሩት በኢህአዴግ ድለላ ያልተረቱ መምህራን መንፈስ ምን እንደሆነ እንዲከታተሉ ግዳጅ ሲሰጣቸው በቀበሌ መዋቅር ሪፖርት ማድረግና የአባላት ምልመላም አከናውነው የስም ዝርዝር እንዲያስተላልፉ « ጥምር » የተሰኘ ተልእኮ የተሰጣቸው መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት ተመረቁ የተባሉ ተማሪዎች በበኩላቸው በተለያዩ የስራ መስኮች እንዲመደቡ የሚደረግ ሲሆን በሚመደቡበት ተቋዋም ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች ውሎ እና አመለካከት መከታተል እንዳለባቸው ተነግሮዋቸው ምደባቸውን እየተጠባበቁ መሆኑም ታውቆዋል፡፡ ለእነዚህ ወጣቶች መደለያ የሚሆን በርካታ ገንዘብ በአነስተኛና ጥቃቅን ብድር ሰጪ ተቋዋማት በኩል አስፈላጊው ድጋፍ እንደሚደረግላቸውና በብረታ ብረት፤ ብሎኬት፤ እንጨት እና ተመሳሳይ ስራዎችን ትሰራላችሁ በማለት ቃል ተገብቶላቸው እንደነበርም ይነገራል፡፡

ወያኔ አሰስ ገሰሱን እያሰባሰበ የአባላት ቁጥር ወደ አምስት ሚሊዮን ደርሶዋል እያለ ቢለፍፍም ከጥቂት ባለስልጣናት በስተቀር በተመደቡበት ቦታ ሁሉ የአባላት ቁጥርን በመጨመርና ጎረቤትን በመሰለል ስራ እንዲሰማሩ የእለት ሪፖርታቸውንም በቀበሌ መዋቅር በሚገኝ የስለላ መዋቅር እንዲያቀርቡ ጥብቅ ትእዛዝ የተሰጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ከፍላጎታቸው አኩዋያ አንድ አዲስ ነገር ቢፈጠር ሊንሸራተቱ ይችላሉ ከአባልነታቸው መውጣታቸው አይቀርም የሚለው ስጋት ግን ለወያኔ የራስ ምታት መሆኑ አልቀረም፡፡ ወያኔ ግራ ሲገባው የአባላትን ማብዛት እንደ ብቸኛ መወጣጫው አድርጎ በመቁጠር ሰራተኞችንና መምህራን በጥቅማ ጥቅም ለመያዝ እላይ ታች እየዘለለ ከመሆኑም በላይ ሰሞኑን ለመምህራን የቤት ኪራይ በሚል የደሞዝ ጭማሪ ማድረጉ ታውቆዋል ፡፡

ከመስከረም 2 ቀን 2002 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ የሚሆን ለመምህራን የደሞዝ ጭማሪ ተብሎ 250 ብር ለቤት ኪራይ በሚል ሽፋን የሰጣቸው ሲሆን ለተቀሩት የመንግስት መስሪያ ቤት ሰራተኞች ግን የዚህ እድል ተቋዋዳሽ ሳያደርጋቸው መቅረቱን ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

በሃገሪቱ በነዳጅ ዋጋ መናር የዶላር ምንዛሪ ባሻቀበበት ከ11 ብር ከ33 ሳንቲም ወደ 12 ብር ከ44 ሳንቲም በወጣበት ወቅት ህዝቡን በመናቅና በጥላቻ በመመልከት በአባልነት ለመዘገባቸው መምህራኖች ሲል ለይቶ በወር የ250 ብር ጭማሪ ማድረጉ ምን ያህል መምህራንን መቆጣጠር እንደፈለገ ያሳያል፡፡

የገዛ ካድሬዎቹ አጋጣሚውን ሲያገኙ እየከዱትና እየኮበለሉ ባለበት በዚህ ወቅት መምህራንን የፖለቲካ ፓርቲው አባል እንዲሆኑ እና የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስብከት ብቻ በመስበክ ታዳጊውን ትውልድ በወያኔ የጎጥና የዘረኝነት ፖሊሲ አጥምዶ በመያዝ ለከፋፍለህ ግዛው እኩይ እቅዱ አስፈጻሚ የሚሆኑ ተከታዮቹን ለማብዛት ሲል የተጠቀመበት ስልት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው ሲልም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

ስለወያኔ ጉዞው ያልገባቸው ባህሪውን ያልተረዱ ምልምል ሰልጣኞች ስራ ላይ ከተሰማሩ አንድ ወር ያልሞላቸው ቢሆንም ለተሰጣቸው እኩይ ተልእኮ ህሊናቸውን በሆዳቸው ቀይረው ታማኝ አገልጋይ እንዲሆኑና ወያኔም እንደፈለገው እንዲጋልብባቸው ሲባል በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር የአገርና የህዝብ አንጡራ ሃብት ከዝርፊያ ባልተናነሰ ሁኔታ ወጪ ተደርጎ እንዲንበሸበሹ፤ የጫት ሱሳቸውንና የማታ መሸታቸውን ወጪ እየሸፈኑ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አመልክቶዋል፡፡

በቅርቡ ለአጭር ስልጠና ተልኮ ወደ አሜሪካ ያቀናው ኤርሚያስ ለገሰ የተባለው ወያኔ እንደወጣ በመቅረት እየማለ የሚገዘትበትን ድርጅት መክዳቱ ታውቆዋል፡፡ ኤርምያስ ለገሰ የበረከት ስምኦን ታናሽ ሆኖ በሚኒስትር ዴኤታነት የመንግስት ኮሙኒኬሽን የተባለውን የፕሮፓጋንዳ ወፍጮ ዘዋሪ እንደነበር ዘገባው አስረድቶዋል ፡፡ ወያኔ እርስ በእርስ ትርምስ በፈጠረበት ሰዓት ያገለግለኛል ብሎ አዲስ ሹመት የሰጠው ግለሰብ ከጉያው ሾልኮ በመክዳቱ በረከት ስምኦንን ጨምሮ በርካታ የወያኔ ባለስልታናት አንጀት ያረረ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልጦዋል